# ስብሐት ለእግዚአብሔር

አዳምና ሔዋን ለዲያብሎስ ድል ተነስተው ከገነት ወጥተው ወደ ምድረ ፋይድ በሚሰደዱበት ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ አም ስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ተሰቅዬ ሙቼ ተነሥቼ አድንሃ ለሁ የሚል ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር ከአዳም እስከ አብርሃም ከአ ብርሃም እስከ ዳዊት ከዳዊት እስከ ልደተ ክርስቶስ ድረስ የነበሩት አበው የዚህን ተስፋ ፍጻሜ ለማ የት ይመኙ ነበር ፤ ነገር ግን ለማየት አልበቁም ።



የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ተወለደልን

በተለይም በሰባት መቶ ዓ. ዓለም ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው ኢሳይያስ "ብርሃን ዓቢይ ሠረቀ ላዕሌሆሙ ለእለ ይነ ብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት" በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ብርሃንን አየ በሞት ጥላ አገርም ለነበሩ ብርሃን ወጣላቸው ካለ በኋላ እንደገና ሕፃን ተወልደ ለነ ወልድ ታውህበ ለነ" ሕፃን ተወል ዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶና ልና ብሉ ከምኞቱ የተነሣ በዘመኑ እንደተፈጸመ አድርጎ ተናገር አል (ኢሳ. ፱. ፪—፯ ።)

ይልቁንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማን በምን እንደሚ ወለድ ሲናገር "ናሁ ድንግል ትፀ ንስ ወትወልድ ወልደ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል" እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳ ለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠ ራዋለች በማለት ግልጥልጥ አድርጎ

፲፫

